# የኢትዮ - ሱዳን ድንበር ማካለል እና መንግሥት የሰጠው መግለጫ

*ከስዬ አብርሃ*

ከጥቂት ዓመታት በፊት አዛውንቱ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ሥዩም መስፍን በተናገረው ላይ አስተያየት ሲሰጡ እግረ መንገዳቸውን «የኢትዮ - ሱዳን ድንበርን የማካለል ሥራ ሊሠራ እየታሰበ መኾኑን» የሚገልጽ መረጃ ጠቀስ አድርገው ነበር:: ከዚያ በፊት መንግሥት ይህን እያሰበ እና እየሠራ መኾኑን ያሳወቀበት ኹኔታ አልነበረም:: ይህን ተከትሎም ይፋዊ የኾነ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መግለጫ ሳይሰጥበት እስከ አሁን ድረስ ቆይቷል::

ሰሞኑን ይኸው ጉዳይ ትልቅ የአገሩ መነጋገሪያ ኾኗል:: በጀርመን ድምፅ ሬዲዮ እና በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የአማርኛ ቋንቋ አገልግሎት ሰፊ ሽፋን አግኝቷል::

የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክትል ርእሰ መስተዳደር አቶ ደመቀ መኮንንን በስልክ አግኝቶ በመንግሥት በኩል ያለውን አቋም ሊያሳውቀን ቢሞክርም የሚረባ መረጃ እና ማብራሪያ ማግኘት አልቻልንም:: ነገሩ እየገፋ ሲመጣ እና ባለሥልጣናቱ ደብቀው ሊደብቁት የማይቻላቸው ሲኾን ግንቦት ሦስት ቀን 2000 ዓ.ም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ ሰጥቶበታል:: እንደዚሁም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም. በነበረው የፓርላማ ልዩ ውሎ መልስ/ማብራሪያ ሰጥቶበታል::

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር «ለእንዲህ ዐይነት መሠረተ ቢስ አሉባልታዎች በየጊዜው ምላሽ መስጠት አላስፈላጊ ቢኾንም «ውሸት ሲደጋገም እውነት ሊመስል ይችላል» ከሚል መግለጫውን እንደ ሰጠ ያሳያል:: የዛሬው አስተያየቴ በዚህ ጉዳይ ላይ ያጠነጥናል::

## «ግጭት ለመፍጠር ኾን ተብሎ የሚደረግ አደገኛ አሻጥር»!?

ይህ አገላለጽ የአገራችንን ድንበር በተመለከተ በተለያዩ የብዙኀን መገናኛዎች ገሃድ የኾነው የሰሞኑ ኹኔታ ወደ አደባባይ በመውጣቱ ያለውን ተቃውሞ ለመግለጽ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተጠቀመበት ነው::

*(ይህ ጽሑፍ አቶ ስዬ አብርሃ በ"አዲስ ነገር" ጋዜጣ ቅጽ 1፣ ቁጥር 32፣ ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓ.ም. ዕትም ከፃፉት ላይ የተወሰደ ነው)* http://www.ethiopiazare.com

አገር ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ ስለዚህ ጉዳይ ለማወቅ የቻለው በዋነኛነት በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የአማርኛ ቋንቋ አገልግሎት እና በጀርመን ድምፅ ሬዲዮ በኩል ነው:: ተቋማቱ በአሜሪካ እና በጀርመን መንግሥታት በጀት የሚተዳደሩ መንግሥታዊ ተቋማት እንደ ኾኑም ይታወቃል:: የየመንግሥታቸውን አቋም እና ፖሊሲ ማንጸባረቃቸው የማይቀር መኾኑ ቢታመንም የአሜሪካ እና የጀርመን መንግሥታት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ እና በሱዳን መንግሥታት መካከል «ግጭት ለመፍጠር ኾን ተብሎ በሚደረግ አደገኛ አሻጥር» ተባባሪ ይኾናሉ ተብሎ ቢገመት የሚቻል አይመስለኝም::

ኢሕአዴግ እና ኢሕአዴግ መራሹ መንግሥት ድንበር ማካለልን የሚያኽል ትልቅ ጉዳይ ይፋ ሳያደርጉ በድብቅ ሲሄዱበት ቆዩና በድንገት በሩ ሲበረገድባቸው ተደናግጠው ለምን ተገለጠ እና ታወቀ ብለው ነው እየጮኹብን ያሉት:: ከታወቀ በኋላም በዚህ ጉዳይ አትናገሩ፣ አትወያዩ እያሉ በማስፈራሪያ እና በዛቻ ሌላ ክልከላ እያበጁብን ነው:: ይህን ብዙ ዘለፋ እና ቃለ ኀይል የተሞላበትን መግለጫ ስሰማ እኔም በድርጅቱ አመራር ውስጥ በነበርኩበት ወቅት ኢሕአዴግ በኢትዮ - ኤርትራ ግንኙነት ዙሪያ ይለው የነበረውን ነገር ነው ያስታወሰኝ::

በመሀል አገር እና በድንበር አካባቢ ሻዕቢያ ሲያደርግ የነበረውን የዝርፊያ፣ አገርን የመዳፈር እና የትንኮሳ ተግባራት የተመለከቱ በርካታ የፓርቲው አባላት እና አባላት ያልኾኑ ዜጎች ድርጊቱን በመቃወም አስተያየታቸውን ይሰጡ ነበር:: ኢሕአዴግ ይህን ለአገር ደኅንነት እና ጥቅም ከመቆርቆር የመነጨውን ገንቢ አስተያየት እና ጥቆማ ወስዶ በወቅቱ ተገቢውን የእርምት እርምጃ በመወሰድ ፈንታ አስተያየቱን የሚያቀርቡትን ዜጎች በመላ «ኾነ ብለው የአትዮ - ኤርትራን ግንኙነት ለማበላሸት የሚፈልጉ ነገር ተንኳሾች» እያለ ይፈርጃቸው እና ያሸማቅቃቸው ነበር:: ከዚህም አልፎ «ነጻነት ያልተዋጠላቸው ነፍጠኞች እና ትምክህተኞች ወይም የእነርሱ አቋም አራማጆች» ይባሉ እንደ ነበር ይታወቃል::

ሚያዝያ 1990 ዓ.ም. ላይ በተጨባጭ የኾነውን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እና የአገር መከላከያ ሰራዊት ያውቁታል:: የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ተፈራ ዋልዋ «ከኤርትራ ጋር ያለው ግንኙነታችን ችግር የለበትም:: በጣም ጥሩ ኹኔታ ላይ ነው» ብለው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ባደረጉ አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው የሻዕቢያ ሜካናይዝድ ኃይል ወደ ባድመ ገብቶ ሚልሻዎቻችንን እና ፖሊሶቻችንን

በታንክ የደፈጠጠው፡፡ «አገርህ ሰላም ነው» ተብሎ ሲነገረው የከረመው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅ ሲባል የነበረው ሻዕቢያ በድንገት «የአገርህን ዳር ድንበር ጥሶ መሬትህን ይዟል፤ ሉዓላዊነትህ ተደፍሯል» የሚል አስደንጋጭ ዜና ነበር የተነገረው፡፡ ይህን አስደንጋጭ ዜና የሰማው የኢትዮጵያ ሕዝብ «እንዲህ ስትለን አልነበረም ወይ?» ብሎ ከኢሕአዴግ ጋር በመወቃቀስ ጊዜ አላጠፋም፤ እምቢ ለዳር ድንበሬ ለሉዓላዊነቴ ብሎ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተነቃነቀ እንጂ፡፡

ወረራው ሲፈጸምብን የአገር መከላከያ ሰራዊታችን የነበረውን ቁመና እንኳን በሥራው ውስጥ የነበረው እና አብዛኛው ዜጋም የሚያውቀው ነው፡፡ ያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ የማያወላውል አቋም ወስዶ ለመከላከያ ሰራዊታችን ባይደርስለት ኖሮ በጦር ሜዳ የተገኘው ውጤት አይገኝም ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገሩ ሉዓላዊነት እና በዳር ድንበሩ ጉዳይ ስሱ ነው፡፡ የፈለገው የብሔር እና የፖለቲካ ልዩነት ይኑር በአገሩ ሉዓላዊነት፣ ነጻነት እና ዳር ድንበር ጉዳይ ላይ ግን በአንድነት ይቆማል፡፡ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያውቅ ሰው ይህን እውነታ በሚገባ ይገነዘባል፡፡ ለአገራችን ህልውና እና ለወደፊት ዕጣ ፈንታዋ ትልቅ ፋይዳ ያለው የአገር ኀሊናዊ ዕሴት መኾኑንም ይገነዘባል፡፡ ታላቅ አክብሮት እና ዋጋ ሊሰጠው የሚገባ በእጃችን ውስጥ ያለ ትልቁ ዕሴታችን ነውና ተንከባክበን ልንይዘው ይገባል፡፡

የአሁኑ የአገሪቱ ገዢዎች ካለፈው ስሕተት በትንሹ እንኳን የተማሩ አይመስልም፡፡ የድንበር ጥያቄ ምን ሊቀሰቅስ እንደሚችል አስቀድሞ ገምቶ ጉዳዩን ግልጽ እና ይፋዊ በኾነ መንገድ መያዝ ሲገባቸው በአጎራባች ክልሎች ካድሬዎች በኩል በድብብቆሽ ሲሄዱበት ቆዩና አሁን በእጃቸው ላይ ፈነዳባቸው፡፡ ይህም ኾኖ አስተውሎት እና አክብሮት የተመላበት መግለጫ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በመስጠት ፈንታ «በእሳት ላ ይ ጭድ. . .» እንዲሉ «ግጭት ለመፍጠር ኾን ተብሎ የሚደረግ አደገኛ አሻጥር» ነው ብለው በጉዳዩ ላይ ሐሳብ የሚሰጡትን ሊያስፈራሩ እና ሊያስበረግጉ ይሞክራሉ፡፡ ይህ አካሄድ ከነባሩ የኢትዮጵያውያን ኀሊናዊ ዕሴት ጋር በቀጥታ የሚላተም በመኾኑ የበለጠ ቁጣ እና ውስጣዊ ውዝግብ ከመፍጠር ያለፈ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም፡፡

## ከዘመነ ሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) ጋር መሄድ ያቃተው የኢሕአዴግ የብዙኀን መገናኛ ፖሊሲ እና የገባበት አጣብቂኝ

መስከረም 1994 ላይ በኒው ዮርክ መንትያ ሕንፃዎች እና በፔንታጎን ሕንፃ ላይ የደረሰው እና ለበርካታ ንጹሐን ወገኖች ሕይወት መጥፋት ምክንያት የኾነው የሽብር አደጋ ከደረሰ ከጥቂት ወራት በኋላ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና የያኔው የኬንያ ፕሬዝዳንት አራፕ ሞይ ወደ ዋይት ኀውስ ቤተ መንግሥት ሄደው ፕሬዝዳንት ቡሽ ዘንድ ቀርበው ነበር፡፡ አቶ መለስ ለወቅቱ የመረጠውን እና በፕሬዝዳንቱ ፊት የተናገሩትን ዋና ዐረፍተ ነገር አስታወሳታለሁ፡፡ አሸባሪዎችን ሲገልጻቸው፡- «እነዚህ ከዘመነ ግሎባላይዜሽን ጋር መጓዝ ያቃታቸው ናቸው» ነበር ያለው አቶ መለስ፡፡

ዛሬ የመረጃ ቴክኖሎጂው በረቀቀበት የግሎባላይዜሽን ዘመን የአገር ውስጥ ሚድያውን በሞኖፖል መያዝ ከጊዜው ጋር የሚሄድ አይደለም፡፡ ይኹንና አቶ መለስ እና ባለሥልጣኖቻቸው የጊዜውን የመረጃ መተላለፍ ሥርዐት በሚቃረን መልኩ ሚድያው በእጃቸው ውስጥ ስለኾነ ቋራ እና መተማ እየኾነ ያለውን የሚነግረን አጥተን ሳንሰማ ከርመናል፡፡ ቋራም፣ መተማም ስልክ አለና ከዚያ ተደውሎ መረጃው አውሮፓ እና አሜሪካ ድረስ የኢትዮጵያ ሬዲዮ እና ፋና ሬድዮ ሊነግሩን ያልፈለጉትን የጀርመን ሬዲዮ ጣቢያ እና የአሜሪካ ሬዲዮ ጣቢያ ነገሩን፡፡ ኢሕአዴግ እንድንሰማው ያልፈለገነውን መረጃ መስማታችን አልቀረም፡፡ እነርሱም ደብቀው የማይደብቁት ነገር ሲኾንባቸው እያንገራገሩም ቢኾን አንዴ መግለጫ ብለው ሌላ ጊዜ ለቀረበ ጥያቄ መልስ ብለው ራሳቸው ይነግሩን ጀመር፡፡

ከእንግዲህ «ሰው አያውቅም፤ ሰው አይሰማም» ብሎ በድብብቆሽ መካድ ጊዜው አልፎበታል፡፡ የሚበጀው መስማቱ እና መታወቁ አይቀርም ብሎ ጉዳዮችን ከጧቱ ጀምሮ ግልጽነት በተሞላበት መንገድ ብቻ ማስኬድ ነው፡፡ ይህ አማራጭ የኋላ ኋላ የሚመጣውን የእሳት ማጥፋት ሥራ ያስቀራል፤ የሕዝብ አመኔታንም ያስገኛል፡፡ ለኢሕአዴግ የሚበጀው አሁን ተይዞ ያለው መንገድ ሳይኾን ከግሎባላይዜሽን ጋር የሚሄደው መንገድ ነው፡፡ አለበለዚያ «ከግሎባላይዜሽን ጋር መሄድ ያልቻሉ» መባልን ያመጣል፡፡

## መንግሥት ከሰጠው ማብራሪያ እስከ አሁን ለማወቅ የቻልነው ምንድን ነው?

እ.ኤ.አ ከ2001 ጀምሮ የድንበር ኮሚሽን እና አንድ ልዩ ኮሚቴ መቋቋማቸውን ሰምተናል፡፡ ይህ እየተሠራ መክረሙን በይፋ የተነገረን እ.አ.አ በ2008 ከሰባት ዓመት በኋላ ነው፡፡

ኢሕአዴግ ከዐዔ ኀይለ ሥላሴ እና ከደርግ ወረስኹት ያለውን የድንበር ጉዳይ ለምን ፓርላማውን እንኳን ሳያሳውቅ ሲሄድበት እንደቆየ አልገለጸልንም:: ሰሞኑን የተፈጠረው ኹኔታ ባይፈጠር ኖሮስ ይገልጽልን ነበር ወይ? የሚል ጥያቄም ያጭራል::

«የድንበር ክለላ የራሱ ሕግ እና ሥርዐት ያለው፣ አንድ መንግሥት እንደ ፈለገ የሚያደርገው ጉዳይ ያለመኾኑ» ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቢነግሩንም ይፋ ሳይደረግ ለአገሪቱ ፓርላማ እንኳን ሳያሳውቅ ለሰባት ዓመት መሉ ሲካሄድ የቆየው ሥራ በምን ሕግ እና ሥርዐት ሲያካሂደው እንደ ቆየ መንግሥት ግልጽ አላደረገልንም::

«ድንበሩን እንደ ገና የማካለሉ ተግባር እንደሚናፈሰው ወሬ ያለቀለት ሳይኾን እየተከናወነ ያለው ወደፊት የወሰን ምልክት ለማስቀመጥ የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሥራን የሚመለከት ነው» ይለናል መግለጫው:: ድንበሩን የማካለል ተግባር በውስጡ በቅደም ተከተል የሚሠሩ ሥራዎች አሉትና ሌሎቹ ሳያልቁ ወደ የ«ወሰን ምልክት ማስቀመጥ» እንደማይኬድ እውነት ነው:: ከዚያ በፊት መሠራት ያለባቸው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መኖራቸውም እውነት ነው:: እነዚህ ግን የድንበር ማካለሉ ተግባር አካላት ናቸው:: እነዚህን ቅድመ ዝግጅት ያላችኋቸውን ሥራዎች እየሠራችሁ ከኾነ የሚናፈሰው ወሬ ትክክል ነው ማለት ነው:: ችካል መትከል የሥራው የመጨረሻ ምዕራፍ ነው:: ይህ ከተሠራ ጉዳዩ አለቀለት፤ ታሪክ ይኾናል ማለት ነው:: ነገር ሳያልቅ በፊት ጉዳዩ ይፋ በመወጣቱ ነው ስሕተት ተሠራ የምትሉት? በድብቅ የጀመራችኹትን ሥራ ጨርሳችሁ ነገር ሁሉ ካለቀለት በኋላ መርዶ ነጋሪ አለመኾናቸው እና አስቀድመው ጉዳዩን ይፋ በማድረጋቸው ነው የአሜሪካ ሬድዮ ጣቢያ እና የጀርመን ሬዲዮ ጣቢያ «እጅግ አጸያፊ አሉባልታ» አናፈሱ ተብለው የተወገዙት?

መግለጫው እስከ አሁን እየተሠራ ባለው ሥራ «አንድም የኢትዮጵያም ኾነ የሱዳን ገበሬ አልተፈናቀለም» ይለናል:: እኛም «የሱዳን ገበሬ ተፈናቀለ» የሚል ዜና አይደለም የሰማነው:: የሱዳን ባለሥልጣናት ራሳቸው «ኢትዮጵያ ለሱዳን መሬት መስጠቷን ተናገሩ» የሚል ዜና ነው የደረሰን:: ሱዳኖች መሬት ተጨምሮላቸው ሲያበቃ እንዴት ተብሎ «የሱዳን ገበሬ ተፈናቀለ» የሚል ዜና ይጠበቃል? እኛ የሰማነው የኢትዮጵያ ገበሬዎች መፈናቀላቸውን፣ ከዚያም አልፎ በሱዳን መንግሥት መታሰራቸውን ነው:: ይህን የሰማነው በጀርመን ሬድዮ ጣቢያ እና በአሜሪካ ሬድዮ ጣቢያ በኩል በቀጥታ ከሰለባዎቹ አንደበት ነው:: ታዲያ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች አይደሉም ማለት ነው ወይስ ሐሰተኛ የሰዎች ድምፅ ነው የሰማነው ?

አቶ መለስ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በፓርላማ ጥያቄ እና መልስ ፕሮግራም ወቅት በዚሁ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ ሲሰጥ ኢንቨስተሮች መፈናቀላቸውን ተናግሯል:: እነዚህ ገበሬዎች አይደሉምን? አብዛኛው የዚያ አካባቢ አራሽ የሚያመርተውን ምርት ለገበያ የሚያቀርብ መኾኑ እየታወቀ አቶ መለስ በአንድ በኩል «አንድም ገበሬ አልተፈናቀለም» በሌላ በኩል ደግሞ «ኢንቨስተሮች ተነሥተዋል» ማለቱ እና ኢንቨስተሮችን በገበሬ ምድብ ለማስገባት ያልፈለገበት ምክንያት ለምን ይኾን? ኢሕአዴግ ለገበሬው የቆመ ስለኾነ «ገበሬው ተፈናቀለ» ቢባል የላቀ ፖለቲካዊ ጉዳት ስለሚያመጣ ጉዳቱን ለመቀነስ ተብሎ ይኾን የቃላት ምርጫ ውስጥ የተገባው?

ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ ይኹን ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ እየተነገረን ያለው የማካለሉ ሥራ እንዳልተከናወነ ነው:: ማካለሉ ባልተከናወነበት ኹኔታ «ያላችኹበት መሬት የኢትዮጵያ መሬት አይደለም እና ልቀቁ» ብሎ ገበሬዎቹ/ኢንቨስተሮቹ እንዲነሡ የተደረገው ታድያ በምን ሐሳብ ነው? «ነገሩ ያለቀለት ጉዳይ አይደለም» እያላችሁ በሌላ በኩል ደግሞ «የሱዳንም የኾነ የኢትዮጵያ ያልኾነ መሬት አለ» ብላችሁ ለመለየት እንዴት ቻላችሁ?

የትኛውን ቃላችሁ እንውሰድ? «አንድም ገበሬ አልተፈናቀለም» ፤ «የድንበር ማካለል ሥራ አልተከናወነም» ወይስ «ማካለል እየተከናወነ ነው:: በዚሁም ምክንያት ኢትዮጵያ መሬት በማስረከቧ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች/ኢንቨስተሮች ተፈናቅለዋል» የሚለውን? ይህም እንደ ባድመ «ለእኛ እንድትኾን ተፈረደልን» ዐይነቱ ጨዋታ ሊኾን ነው እንዴ?

## <u>ኢሕአዴግ በድንበሩ ጉዳይ ፓርላማውን ሳይቀር አለማሳወቁ ከምን የተነሣ ሊኾን ይችላል?</u>

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያለው አብላጫ ድምፅ የኢሕአዴግ እና የአጋሮቹ ድርጅቶች መኾኑ፣ የፓርላማው የውስጥ ደንብ እጅጉን ክልከላ የበዛበት መኾኑ እና ኢሕአዴግ አባላቱን የሚቆጣጠርበት ዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት የሚለው መርሕ ከወታደራዊ የእዝ ሥርዐት ያልተለየ መኾኑ ሲታሰብ አንድ ጉዳይ በፓርላማ ስለ ቀረበ ብቻ መቋጫው ላይ ኢሕአዴግ ከሚፈልገው መንገድ ውጭ ይሄዳል ተብሎ የማይታሰብ ነው::

ጉዳዩ በፓርላማ በመቅረቡ ግፋ ቢል በጉዳዩ ላይ ተቃዋሚዎች ሐሳባቸውን ለማሰማት ዕድል ያገኛሉ:: ከዚያ ባሻገር ደግሞ ጉዳዩ በፓርላማ ሲነሣ ይፋዊነት ያገኛል:: ኢሕአዴግ

ጉዳዩን ሰባት ዓመት ሙሉ ሲያካሂደው መቆየቱ እና በዚህ ጊዜ ውስጥ አንዳችም ጊዜ ፓርላማውን ለማሳወቅ ያለመፈለጉ ምክንያቶች ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ወይም ሁለቱ ሊኾኑ ይችላሉ ብዬ እገምታለሁ::

አንደኛው ሊኾን የሚችለው ምክንያት ኢሕአዴግ በዚህ ጉዳይ ላይ የገዛ አባላቱን ሳይቀር ተጠራጥሯል የሚል ነው:: በዴሞክራሲያዊ ማእከልነት መርሕ ተገዝተው የኢሕአዴግ አባላት በብዙ ጉዳዮች በመደዳ እጃቸውን እንደሚያወጡ ቢታወቅም ይህ ጉዳይ ግን ለየት ያለ ነው:: በጣም ስሱ የኾነው የአገር ዳር ድንበር እና የአገር ሉዓላዊነት ጉዳይ ነው:: አንዳንድ አባላት ሊሸከሙት ከሚገባቸው በላይ ኾኖባቸው ከድርጅቱ መርሕ በማፈንገጥ ኅሊናቸው የመራቸውን እና ለአገር ይበጃል ብለው ያመኑበትን አቋም ሊያራምዱ ይችላሉ::

እንደዚህ ያለ ኹኔታ የመከሠቱ ዕድል ጠባብ ቢኾንም ሊኾን የማይችል ነው የሚባል ግን አይደለም:: ደፍረው ይህን አካሄድ የሚመርጡት የኢሕአዴግ የፓርላማ አባላት ደግሞ ጥቂት ሊኾኑ ይችላሉ:: ቁም ነገሩ ግን መብዛታቸው ላይ አይደለም:: ዋናው ነገር ምሳሌነቱ ነው:: በአሁኑ ወቅት በተለይ ደግሞ በዚህ ጉዳይ ላይ «በቃኝ» የሚል የኢሕአዴግ የፓርላማ አባላት መኖራቸው እና ይፋ መውጣታቸው የሚኖረው ፋይዳ ከሰዎቹ አጠቃላይ ቁጥር በላይ ነው:: ኢሕአዴግ ይህን አሣምሮ ይገነዘባል::

በዚህ ጉዳይ ላይ በዐፄ ኀይለ ሥላሴ ፓርላማ መካከል የተነሣውን ግርግር ያስታውሷል:: የሻለቃ ጉዊን መስመር ስለ ተባለው መስመር ሰሞኑን በተደጋጋሚ ሰምተናል:: ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም በአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ ከሰጡት ማብራሪያ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ከጋላባት ወደ ደቡብ ባለው የሻለቃ ጉዊን መስመር ላይ ብዙ ችግር የለም:: ከጋላባት ወደ ሰሜን በሚሄደው የመስመሩ ክፍል ላይ ግን ችግር አለ:: በዚህኛው የመስመሩ ክፍል ላይ ሁለት የጉዊን መስመሮች ናቸው ያሉት:: አንዱ ወደ ምዕራብ ገባ ያለ እና የኢትዮጵያን መሬት የሚያሰፋ ሁለተኛው ወደ ምሥራቅ ገባ ያለ እና የአትዮጵያን መሬት የማያሳንስ ነው:: እ.ኤ.አ በ1972 ዓ.ም የንጉሡ መንግሥት ተቀበለው የተባለው ሁለተኛው መስመር መኾኑ ሲሰማ የንጉሡ ፓርላማ ተቃውሞ እንዳሥነሳ እና ንጉሡ ችግር እንዳጋጠማቸው አዛውንቱ ፕሮፌሰር ገልጸውልናል:: እኛ ያኔ በልጅነታችን እንደ ሰማነው ከኾነማ ንጉሡ የደቡብ ሱዳን ዐማፅያንን እንዳይደግፉ የያኔው የሱዳኑ ፕሬዝዳንት ጃዕፈር ኒሜሪም የኤርትራ ዐማፅያንን እንዳይደግፉ ተስማምተው ነበር:: ንጉሡም አንደኛዋን የጉዊን አማራጭ ችላ ያሏት በዚህ ምክንያት ነው ተብሎ ይታማል::

*(ይህ ጽሑፍ አቶ ስዬ አብርሃ በ"አዲስ ነገር" ጋዜጣ ቅጽ 1፣ ቁጥር 32፣ ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓ.ም. ዕትም ከፃፉት ላይ የተወሰደ ነው)* http://www.ethiopiazare.com

አሁን ኢሕአዴግ በአብላጫ የሚቆጣጠረው ፓርላማ በፓርቲው ሊቀ መንበር በአቶ መለስ ሙሉ ቁጥጥር ሥር እንደ ኾነ አሌ የማይባል ነው። የያኔው የኢትዮጵያ ፓርላማም በዐፄው መዳፍ ውስጥ እንደ ነበር የሚያከራክር አይደለም። በአገር ዳር ድንበር ላይ የንጉሡ ፓርላማ ንጉሡ ከፈቀዱት የተለየ አቋም እንዳላራመደ ሁሉ የኢሕአዴግ ፓርላማ አባላት ቢያንስ ከፊሉ ከሊቀ መንበራቸው የተለየ አቋም ያራምዳሉ ለማለት አይቻልም።

ሁለተኛ ምክንያት ይኾናል ብዬ የምገምተው:- ጉዳዩ ራሱ በፓርላማ ተነሥቶ በይፋ የመወያያ ርእስ መኾኑ፣ በዚህም አማካይነት ሕዝቡ ስለ ገዳዩ ለማወቅ ዕድል ማግኘቱ በራሱ ለገዢው ፓርቲ ስጋት የመፍጠር አቅሙ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገር ነጻነት እና ሉዓላዊነት ጉዳይ እጅግ ስሱ ከመኾኑ የተነሳ ኢሕአዴግን በዳር ድንበር ጉዳይ አያምነውም። በእንዲህ ያለ ኹኔታ በፓርላማው ለውይይት መቅረቡ የመጨረሻ ውሳኔው ላይ ለውጥ ባያመጣም ቢያንስ ተቃዋሚዎች ሐሳባቸውን የመግለጽ ዕድል ያገኛሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ከውይይቱ መረጃም ኾነ ሐሳብ ያገኛል። በዚህ ጉዳይ ላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሐሳባቸውን በግልጽ መናገራቸው ምን ያህል ኢሕአዴግን እንደሚያሰጋው በግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም ውሎው የታየው ክልከላ ግልጽ ማሳያ ነው። ይህ ጉዳይ ትልቅ የሕዝብ አጀንዳ ኾኖ የሕዝብን ስሜት እና ተቃውሞ ሊቀሰቅስብኝ ይችላል ከሚል ስጋት በመነሳት ሊኾን ይችላል ሰባት ዓመት ሙሉ አገር ሳያውቅ ሲያስኬደው የቆየው።

ፓርላማውን ሳያማክር ሲያስኬደው የቆየውን ጉዳይ «የአገራችንን ሉዓላዊነት ባስጠበቀ፣ ሕዝቡን ባሳተፈ መልኩ እንዲቋጭ ካለው ጽኑ አቋም በመነሣት በጋራ የድንበር ኮሚሽኑ እና በልዩ ኮሚቴው ውስጥ የሱዳን ተጎራባች የኾኑ ክልሎች በአባልነት እንዲሳተፉ» መደረጉን ይገልጻል። መግለጫው አክሎም «የአካባቢው ነዋሪዎች በቀጥታ እንዲሁም በተወካዮቻቸው አማካይነት በሥራው የተሳተፉ ሲኾን ግልጽ ውይይትም በየጊዜው ተካሂዷል። በመኾኑም ጉዳዩ ከሕዝብ የተደበቀ አስመስሎ ለማቅረብ የሚደረገው ሙከራ መሠረተ ቢስ ብቻ ሳይኾን አጎራባች በኾኑ የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች መካከል ግጭት ለመፍጠር የታቀደ መኾኑ አያጠራጥርም።» ይለናል።

በኢሕአዴግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር የሕዝብ ተሳትፎ ማለት ይህ ነው። የአገር ድንበር ጉዳይ መላ ኢትዮጵያውያንን የሚመለከት እንጂ አጎራባች ክልሎችን ብቻ የሚመለከት አይደለም። መላ ኢትዮጵያውያንን እንዲወክል ኾኖ የተቋቋመው ደግሞ

*(ይህ ጽሑፍ አቶ ስዩ አብርሃ በ"አዲስ ነገር" ጋዜጣ ቅጽ 1፣ ቁጥር 32፣ ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓ.ም. ዕትም ከፃፉት ላይ የተወሰደ ነው)* http://www.ethiopiazare.com

የፌዴራል የተወካዮች ምክር ቤት ብቻ ነው:: በአገር ዳር ድንበር ጉዳይ ላይ እኛን ኢትዮጵያውያንን የሚወክል ሌላ ተቋም የለም:: እዚህ ላይ ያለው ዋና ጥያቄ ኢሕአዴግ በዚህ ጉዳይ ላይ ፓርላማው ራሱ በቀጥታ እንዲወያይበት አላደረገም ነው:: ይህ አለመደረጉ ሂደቱን ያለ ጥርጥር ከሕዝብ የተደበቀ ያደርገዋል:: ይህ ባልተደረገበት ኹኔታ «በተወካዮቻቸው አማካይነት በሥራው የተሳተፉ ሲኾን ግልጽ ውይይትም በየጊዜው ተካሂዷል» መባሉ በራሱ ሕገ መንግሥታዊ መሠረት የሌለው አባባል ነው::

ባድመ በትግራይ ክልል ውስጥ ነው ያለው:: የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በባድመ ላይ ያለው ሥልጣን እንደ ማንኛውም የትግራይ አካባቢ ባድመንም ማስተዳደር ነው:: «ባድመ የኤርትራ ነው» ብሎ ለኤርትራ ለመስጠት መወሰን የእርሱ ሥልጣን አይደለም:: ባድመ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ መሬት ነው:: ይህን በሚመለከት ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው ሕገ መንግሥታዊው ተቋም የፌዴራል ሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ነው:: ኢትዮጵያን እና ሱዳንን በሚያዋስነው አካባቢ ያለ ትንሽ መሬትም ቢኾን «የኢትዮጵያ ነው ወይስ የሱዳን ነው?» የሚለው የሚወሰነው በፌዴራል ደረጃ እንጂ የሱዳን አጎራባች በኾኑ ክልሎች ብቻ ሊኾን አይችልም::

የገዛ ፓርላማውን ለማሳተፍ ያልደፈረው ኢሕአዴግ «አጎራባች ክልሎች ተሳትፈውበታል::. . . ጉዳዩ የአገራችንን ጥቅም ባስጠበቀ እና ሕዝብን ባሳተፈ መልኩ እንዲቀጥል አድርጎልናል:: ምንም ስሕተት አልተሠራም» ከማለቱም ባሻገር «ብቻዬን ያደረግኹት አይደለም፤» ብሎ አጎራባች ክልሎችንም የሐላፊነቱ እና የተጠያቂነቱ አባሪ ሊያደርጋቸው እየሞከረ ነው:: ይህ የሚሠራ ስልት አይደለም:: ሕገ መንግሥታዊ ባልኾነ መብቱ ገብቶ ሲዋትት ስሕተት አልሠራም ማለት ባይቻልም ዋናው ተጠያቂ ግን ሊኾን አይችልም::

ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሰጠው መግለጫ ተጠያቂነቱን ወደ አጎራባች ክልሎች ብቻ ሳይኾን ወደ ዐፄ ኀይለ ሥላሴ እና ወደ መንግሥቱ ኀይለ ማርያም ለመግፋት የፈለገ ይመስላል:: በዐፄ ኀይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ እና ሱዳን መንግሥታት እ.ኤ.አ በ1972 ድንበሩ እንደ ገና እንዲካለል ስምምነት መፈረሙን ኾኖም በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1966 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ በመምጣቱ ጉዳዩ እልባት ሳያገኝ መቅረቱን፣ በደርግ ዘመን ደግሞ በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የተጀመረውን ዳር ለማድረስ እ.ኤ.አ በ1980 ዓ.ም ላይ ስምምነት ተደርሶ ሰፊ ዝግጅት ተደርጎ የነበረ ቢኾንም ጉዳዩ እልባት ሳያገኝ ደርግ ከሥልጣን በመወረዱ የኤ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት ይህን መቋጫ

ሳያገኝ የቆየውን «ካለፉት መንግሥታት የወረስኹት» የሚለውን የድንበር ጉዳይ እልባት ለመስጠት ውሳኔ ላይ መድረሱን መግለጫው ነግሮናል።

በዐፄው ይኹን በኮሎኔሉ ዘመን ተደረሰ ስለተባለው ስምምነት ይዘት የሚታወቅ ነገር የለም፤ ስምምነት ኖረ አልኖረ ወደ ተግባር የተሸጋገረ ምንም ነገር የለም፤ ዐፄው ይኹን ኮሎኔሉ በሥልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት ተግባራዊ ያደረጉት የድንበር ማካለል የለም። በመኾኑም አሁን ኢሕአዴግ ተግባራዊ እያደረገ ላለው የድንበር ማካለል ውሳኔ ተጠያቂው እርሱ ራሱ እንጂ ዐፄው ሊኾኑ አይችሉም። ደግሞስ ከመቼ ወዲህ ነው ኢሕአዴግ የደርግ እና የዐፄው የወራሽነት ሸክም ክብዶት መጨነቅ የጀመረው። ለዚያውም እነርሱ ራሳቸው ተግባራዊ ላላደረጉት ስምምነት።

በዚህ ጉዳይ ውሳኔ እየሰጠ ያለው ኤ..ፌ.ዴ.ሪም አይደለም፤ የኤ.ፌ.ዴ.ሪ ፓርላማ ሳያውቀው እና ሳይመክርበት ነውና እየተከናወነ ያለው። «ለድንበሩ ጉዳይ እልባት ለመስጠት» ውሳኔ ሰጥቶ ለተግባራዊነቱ እየተንቀሳቀሰ ያለው በኢሕአዴግ ሊቀ መንበር እና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠ/ሚ/ር አቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው ሕግ አስፈጻሚው አካል ብቻ ነው። ተጠያቂነቱ ከዚያ ላይ ያቆማል፤ ወደ ታች ወደ አጎራባች ክልሎች አይወርድም፤ ወደ ኋላ ወደ ዐፄው እና ኮሎኔሉ አይመለስም።

## «የሱዳን መንግሥት አርቆ አስተዋይነት . . .»

አቶ መለስ በአንድ በኩል «ድንበር አልተካለልንም» እያለ በሌላ በኩል ደግሞ የሱዳን መሬት ውስጥ የሰፈሩ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች (ኢንቨስተሮች) መኖራቸውን እርግጠኛ ኾኖ ነግሮናል። ከዚህ ተነሥቶ ኢትዮጵያውያን በሱዳን መሬት መስፈራቸው እውነት ኾኖ ሱዳኖች እነዚህ ኢትዮጵያውያን «እንዳይፈናቀሉ መስማማታቸውን» በመጥቀስ የእነርሱን አርቆ አስተዋይነት ሲያወድስ ተሰምቷል። የኢትዮጵያ መንግሥት ከሱዳኖች ጋር የሚያደርገው ድርድር «የእኔ የእኔ ነው፤ የአንተን እንካፈል» የሚል መርሕ የተከተለ መኾኑን ነግሮናል። ይህን ይበል እንጂ በዚህ እርሱ «የሱዳን ግዛት ነው» ባለው መሬት ሲያርሱ የነበሩ ኢንቨስተሮች ሱዳኖች «የእኛ የእኛ ነው» ስላሉ እንዳስለቀቋቸው እና በቦታቸው የራሳቸውን ኢንቨስተሮች እንዳስገቡ ነግሮናል። የእርሻ መሬት ችግር የለባቸውም የተባለላቸው ሱዳኖች «ምነው ታዲያ የእኛን ኢንቨስተሮች ገፈተሩ?» የሚለው ጥያቄ አልተመለሰም።

ሱዳኖች አርቆ አስተዋይ ጎረቤት እንዲኾኑ እኔም እመኛለሁ፤ ተስፋም አደርጋለሁ:: ይህን የምመኘው ግን የእነርሱ የኾነውን «የእኛም ነው» ስላልን እሺ እንዲሉን አይደለም:: እኔ የሱዳኖች አርቆ አስተዋይነት እንዲኖር የምመኘው በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ በጸጥታ ችግሮች ተወጥሮ ያለው የአቶ መለስ መንግሥት ካለበት ኹኔታ አንጻር «የጠየቅነውን እሺ ይሉናል» ብለን እሺታን ስላገኙ ብቻ የማይገባቸውን እና የእኛ የኾነውን መሬት እንዳይወስዱ ነው::

ይህ ኹኔታ ነፍሳቸውን ይማርና አዛውንቱ የቀድሞው የጅቡቲ ፕሬዝዳንት ሐሰን ጉሌድ ኦፕቲዶን ለሪፖርተር ጋዜጣ ቃለ መጠይቅ የሰጡ ጊዜ የተናገሩትን ያስታውሰኛል:: በወቅቱ ሻዕቢያ ኢትዮጵያን ከወረረ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነበር እና ወዳጅ የተባለው ኢሳይያስ ወራሪ ኾኖ መገኘቱን ግምት ውስጥ ያስገባ ይመስላል የአዛውንቱ ንግግር:: ጋዜጠኛው «የኢትዮጵያን ጠቅላይ ሚኒስትር ይወዷቸዋል ወይ?» ብሎ የጠየቃቸው ይመስለኛል:: «የኢትዮጵያ መሪ በመኾናቸው አከብራቸዋለሁ» አሉ መውደድ አለመውደድ በሌለበት ሲመልሱ:: አያይዘው ግን «የአገሮች መሪዎች ለወዳጅነታቸው ሲሉ ሐላፊነታቸውን ሳይወጡ ቢቀሩ ለሚከተለው ችግር ዋጋውን የሚከፍለው የአገራቸው ሕዝብ ነው» ብለው ነበር::

ኢትዮጵያ እና ሱዳን በአፍሪካ ቀንድ ሁለት ታላላቅ አገሮች ናቸው:: ይህ እንደ ተጠበቀ ኾኖ በሁለቱም አገሮች መካከል የሚገነባው የመልካም ጉርብትና እና የአብሮ ማደግ ድልድይ በሁለት አገሮች እና ሕዝቦቻቸው ዘላቂ ጥቅም እንጂ በሰሞነኛ የመሪዎች የሞቅ ሞቅ ግንኙነት ላይ መመሥረት የለበትም እላለሁ:: ሱዳኖች ካለፈው የ17 ዓመት የበሽር እና የመለስ ወዳጅነት የተማሩት ነገር ይኖራል: አጋጣሚ አገኘን ብለው በኢትዮጵያ መሠረታዊ ጥቅም እና ሉዓላዊነት ላይ አንዳች አሜከላ ቢተክሉ ግን የኋላ ኋላ ነገሩን «አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ» እንደሚኾን አጥብቀው ሊገነዘቡ ይገባል::

ይህን እያልኹ ያለኹት ያለምክንያት አይደለም:: ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ሳይገባ በፊት የምዕራብ ጎንደር እና ምዕራብ ትግራይ ቆላማ አካባቢዎች በርከት ላሉ ዓመታት የደርግ ጦር ለቋቸው ነበር:: ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ የሽግግር መንግሥት እንደ ተመሠረተ በአካባቢው ሰራዊት አላሰፈርንም ነበር:: በዚህ ወቅት ተጓዳኝ ክሥተቶች ተከሥተዋል::

*(ይህ ጽሑፍ አቶ ስዩ አብርሃ በ"አዲስ ነገር" ጋዜጣ ቅጽ 1፣ ቁጥር 32፣ ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓ.ም. ዕትም ከፃፉት ላይ የተወሰደ ነው)* http://www.ethiopiazare.com

በአንድ በኩል በጦርነቱ ምክንያት ተስተጓጉሎ የቆየው የዚህ ቀጣና የእርሻ እንቅስቃሴ ማንሰራራት ጀመረ:: ለበርካታ ዓመታት ባድማ ኾኖ የነበረው ማሳ እና ተጥለው የቆዩት አሮጌ የኢትዮጵያ ትራክተሮች መላወስ ጀመሩ:: በርካታ ኢትዮጵያውያን ለዚሁ ሥራ ወደ አካባቢው ተመለሱ:: በሌላ በኩል ደግሞ የሱዳን መንግሥት ይህን የጥበቃ ኬላዎች ያለመኖር ኹኔታ በመጠቀም ሰራዊቱን ወደዚህ ቀጣና ማስገባቱን ቀጠለ:: ሱዳናውያን አራሾች የሰራዊታቸውን ኮቴ እየተከተሉ መጠጋት ጀመሩ:: ባለቤት የሌለው መሬት አገኘን ብለው ደኑን ማጥፋት፣ የእርሻ መሬቱን እንዳሻቸው መያዝ ቀጠሉ::

የሽግግር መንግሥት ተመሥርቶ በጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ የሚመራ የሚኒስትሮች ልኡክ ወደ ሱዳን ሲሄድ ከሄዱት ሚኒስትሮች መካከል አንዱ ነበርኩ:: በዚህ የሞቀ ወዳጅነት ወቅት ሱዳኖች ይዘውት የወጡት ትልቁ አጀንዳ «ድንበር እንካለል» የሚል ነበር:: እኛ በዚህ ጉዳይ ለመነጋገር ዝግጁ አልነበርንም:: ስለዚህ የኢትዮጵያ እና ሱዳን ድንበርም የጠበቀ ዕውቀት አልነበረንም:: እነርሱ ግን ስለ ጉዳዩ በደንብ የሚያውቁ ባለሞያዎች እና ሰነዶችን ይዘው ነበር የጠበቁን:: እኛም እሺ ወይም እምቢ ሳንል ጉዳዩን ገሸሽ በማድረግ ውይይታችንን በሌሎች ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ብዙ ጥረት ብናደርግም አጀንዳውን ከመከላከያ እና ጸጥታ ጉዳይ ጋር በማያያዝ ነገሩን የማይታለፍ ለማድረግ መፈለጋቸውን ስንገነዘብ እቅጩን መናገር ነበረብን:: ባላጠናነው እና ባላወቅነው ጉዳይ ላይ አሁኑኑ ድንበር ይከለል ማለት አንችልም:: የሽግግር መንግሥት በመኾናችንም ድንበር የማካለሉ ውክልና (ማንዴት) የለንም አልናቸው:: ነገሩም በዚሁ ቆመ::

ይኽም ኾኖ ሱዳኖች በድንበር አካባቢ የጀመሩትን ጉዳይ አላቆሙም:: ይባስ ብለው በእርሻ ሥራ መቋቋም የጀመሩትን ኢትዮጵያውያን ገበሬዎችን መተናኮል እና መጋፋት ጀመሩ:: ይህ ኹኔታ እየባሰበት በመሄዱ ውሱን የመከላከያ ኀይል በዚሁ አካባቢ በማስፈር ቀስ በቀስ ይህንኑ ማጠናከር ጀመርን:: ሰራዊቱ ይህን በአራሾች ላይ የሚደርሰውን በደል እና በዐይናችን ፊት የሚደርሰውን ውድመት መቃወም ጀመረ:: አንድ ቀን በዚህ አካባቢ የተመደበው የመከላከያ ሰራዊታችን አዛዥ የጽሑፍ መልእክቱን አስይዞ አቻው ወደ ኾነው የሱዳን ጦር አዛዥ አንድ መልእክተኛ ጓድ ይልካል:: የተላከው ጓድ የተደረገለት አቀባበል የወዳጅ አገር ሰራዊት አቀባበል አልነበረም:: ኑ ብለው ተቀብለው ትጥቃቸውን አስፈትተው አረዷቸው:: ይህ ድፍረት እና ጭካኔ እንደ ተፈጸመ ሰራዊታችን አይምሬ የአጸፋ እርምጃ ወስዶ በአካባቢው የነበረው ጦር እንደ ወጣ ቀረ:: እኔ በሐላፊነት እስከ ነበርኹበት ጊዜ ድረስ ሱዳኖቹ ወደዚህ አካባቢ ተተኪ ሰራዊት አልላኩም::

*(ይህ ጽሑፍ አቶ ስዬ አብርሃ በ"አዲስ ነገር" ጋዜጣ ቅጽ 1፣ ቁጥር 32፣ ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓ.ም. ዕትም ከፃፉት ላይ የተወሰደ ነው)* http://www.ethiopiazare.com

አቶ መለስ ሰራዊታችን በ1995/1996 አካባቢ የወሰደው ማጥቃት ብሎ የገለጸው ይህንኑ የአጸፋ እርምጃ ነው። ይህን አካባቢ ሰራዊታችን በወሰደው የአጸፋ ርምጃ ምክንያት በእጃችን የገባ የእኛ ያልኾነ መሬት አድርጎ ማቅረቡ ግን ትክክል አይደለም። የሱዳን ወታደሮች እና እነርሱን ተከትለው የመጡት የሱዳን አራሾች ወደዚህ ቀጣና የመጠጋታቸው ታሪክ ከፍ ብሎ ከገለጽኹት የነገሮች አንድነት ጋር የተያያዘ ነውና ድንበር ሳይካለል በፊት እንደዚህ ብሎ ፍርድ መስጠት አይገባውም ነበር።

የአቶ መለስ መንግሥት ከኤርትራ እና ኢትዮጵያ ድንበር ክርክር ጋር በተያያዘ በአንዳንድ የጾረና እና የአካባቢዋ ቦታዎች ላይ ለኤርትራ ምስክርነት መስጠቱ እና የሄጉ ኮሚሽን በዚሁ ተመሥርቶ እነዚህ አካባቢዎችን ለኤርትራ እንዲሰጡ መወሰኑን ከኮሚሽኑ ሪፖርት ለመገንዘብ ችለናል። አሁንም በአንድ በኩል «ድንበር አልተካለልንም» እየተባለ በሌላ በኩል ደግሞ «ሰራዊታችን በወሰደው ማጥቃት ምክንያት የእኛ አራሾች ገብተውበት ሲጠቀሙበት የቆየ የእኛ ያልኾነ መሬት ነው» ብሎ አስቀድሞ በኢትዮጵያ ላይ እየመሰከረ ነው። አቶ መለስ ስለ ሱዳኖች አርቆ አስተዋይነት ከመናገሩ በፊት ስለ ገዛ ራሱ አስተውሎት ቆም ብሎ ቢጠይቅ ይሻል ነበር።

*(ይህ ጽሑፍ አቶ ስዩ አብርሃ በ"አዲስ ነገር" ጋዜጣ ቅጽ 1፣ ቁጥር 32፣ ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓ.ም. ዕትም ከፃፉት ላይ የተወሰደ ነው)* http://www.ethiopiazare.com